# የያዕቆብ መልእክት

**1** የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ የሆነው ያዕቆብ፤ ለተበተኑ ለዐሥራ ሁለቱ ነገዶች፤

ሰላም ለእናንተ ይሁን።

## መከራና ፈተና

2ወንድሞቼ ሆይ፤ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፤ 3ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ። 4ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉኣን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም። 5ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጐድለው፣ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል። 6ዳሩ ግን ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ ምክንያቱም የሚጠራጠር ሰው በነፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ የባሕር ማዕበል ነው። 7ያ ሰው፣ ከጌታ አንዳች ነገር አገኛለሁ ብሎ አያስብ፤ 8እርሱ በሁለት ሐሳብ የተያዘና በመንገዱ ሁሉ የሚወላውል ነው።

9ዝቅ ያለው ወንድም ከፍ በማለቱ ይመካ። 10ባለጠጋውም ዝቅ በማለቱ ይመካ፤ እንደ ሣር አበባ ይረግፋልና። 11ፀሓይ በነዲድ ሙቀቷ ወጥታ ሣሩን ታጠወልጋለችና፤ አበባው ይረግፋል፤ ውበቱም ይጠፋል፤ እንዲሁም ባለጠጋ በዕለት ተግባሩ ሲዋትት ሳለ ይጠፋል።

12በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ፣ የሕይወትን አክሊል ያገኛል።

13ማንም ሲፈተን፣ “እግዚአብሔር ፈተነኝ” አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም፤ 14ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው። 15ምኞትም ከፀነሰች በኋላ ኀጢአትን ትወልዳለች፤ ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።

16የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ አትታለሉ። 17በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከላይ ከሰማይ ብርሃናት አባት ይወርዳሉ፤ በእርሱ ዘንድ መለዋወጥ፣ ከመዞር የተነሣ የሚያርፍ ጥላም የለም። 18የፍጥረቱ በኵራት እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት ቃል ወለደን።

## ሰምቶ በሥራ ላይ ማዋል

19የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ይህን አስተውሉ፤ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣ ለመናገር የዘገየ፣ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤ 20የሰው ቍጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አያመጣምና። 21ስለዚህ ርኵሰትንና ተንሰራፍቶ የሚገኘውን ክፋትን አስወግዳችሁ ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን፣ በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በትሕትና ተቀበሉ።

22ቃሉ የሚናገረውን አድርጉ እንጂ ሰሚዎች ብቻ ሆናችሁ ራሳችሁን አታታልሉ። 23ቃሉን የሚሰማ፣ ነገር ግን የሚለውን የማይፈጽም ሰው ፊቱን በመስተዋት እንደሚያይ ሰው ነው፤ 24ራሱንም አይቶ ይሄዳል፤ ወዲያውም ምን እንደሚመስል ይረሳል፤ 25ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹም ሕግ ተመልክቶ የሚጸና፣ የሰማውን የሚያደርግና የማይረሳ ሰው በሥራው የተባረከ ይሆናል።

26አንደበቱን ሳይገታ፣ ልቡን እያሳተ ሃይማኖተኛ ነኝ የሚል ሰው፣ ራሱን ያታልላል፤ ሃይማኖቱም ከንቱ ነው። 27በእግዚአብሔር አብ ፊት ንጹሕና ነውር የሌለበት ሃይማኖት ይህ ነው፤ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆችና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች በችግራቸው መርዳትና ከዓለም ርኵሰት ራስን መጠበቅ ነው።

## አድልዎ ማድረግ አይገባም

**2** ወንድሞቼ ሆይ፤ ክቡር በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ እንደ መሆናችሁ አድልዎ አታድርጉ። 2የወርቅ ቀለበት ያደረገና ያማረ ልብስ የለበሰ ሰው ወደ ጉባኤያችሁ ቢገባ እንዲሁም ያደፈ ልብስ የለበሰ ድኻ ሰው ቢገባ፣ 3ያማረ ልብስ ለለበሰው የተለየ አክብሮት በማሳየት፣ “ለአንተ የሚሆን መልካም መቀመጫ ይኸውልህ” ብትሉትና ድኻውን ግን፣ “አንተ በዚያ ቁም” ወይም “ከእግሬ በታች በወለሉ ላይ ተቀመጥ” ብትሉት፣ 4በመካከላችሁ አድልዎ ማድረጋችሁ አይደለምን? ደግሞስ በክፉ ሐሳብ የተያዛችሁ ፈራጆች መሆናችሁ አይደለምን?

5የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ስሙ፤ እግዚአብሔር በእምነት ባለጠጋ እንዲሆኑና እርሱን ለሚወዱም ተስፋ የተሰጣቸውን

1፥1 ዘዳ32፥26፤ ዮሐ7፥35፤ ሐሥ15፥13፡23፤26፥7፤ሮሜ1፥1፤ ቲቶ1፥1፤1ጴጥ1፥1
1፥2 ቀ፦12፤ ማቴ5፥12፤ ዕብ10፥34፤12፥11
1፥3 ዕብ10፥36፤ 1ጴጥ1፥7
1፥4 1ቆሮ2፥6
1፥5 1ነገ3፥9፡10፤ መዝ51፥6፤ምሳ2፥3-6፤ ዳን1፥17፤2፥21፤ ማቴ7፥7
1፥6 ማቴ21፥21፤ ማር11፥24
1፥8 መዝ119፥113፤ ያዕ4፥8፤2ጴጥ2፥14
1፥9 ማቴ23፥12
1፥10 ኢዮ14፥2፤ መዝ103፥15፡16፤ ኢሳ40፥6፡7፤ 1ቆሮ7፥31፤ 1ጴጥ1፥24
1፥11 መዝ102፥4፡11፤ ኢሳ40፥6፡8፤ ማቴ20፥12
1፥12 ቀ፦2፤ዘፍ22፥1፤ ዘፀ20፥6፤1ቆሮ2፥9፤ 8፥3፤9፥25፤ያዕ2፥5፤ 5፥11፤1ጴጥ3፥14
1፥14 ምሳ19፥3
1፥15 ዘፍ3፥6፤ ኢዮ15፥35፤መዝ7፥14፤ ኢሳ59፥4፤ሮሜ6፥23
1፥16 ቀ፦19፤ 1ቆሮ6፥9፤ያዕ2፥5
1፥17 ዘፍ1፥16፤ ዘኍ23፥19፤መዝ85፥12፤ 102፥27፤136፥7፤ ዳን2፥22፤ሚል3፥6፤ ዮሐ3፥27፤ያዕ3፥15፡17፤1ዮሐ1፥5
1፥18 ኤር2፥3፤ ዮሐ1፥13፤2ጢሞ2፥15፤ ራእ14፥4
1፥19 ቀ፦16፤ ምሳ10፥19፤ያዕ2፥5፤ 3፥3-12
1፥20 ማቴ5፥22
1፥21 ኤፌ1፥13፤ 4፥22
1፥22 ማቴ7፥21፤ ያዕ2፥14-20
1፥25 መዝ19፥7፤ ዮሐ8፥32፤13፥17፤ ገላ2፥4፤ያዕ2፥12
1፥26 መዝ34፥13፤ 39፥1፤141፥3፤ ያዕ3፥2-12፤ 1ጴጥ3፥10
1፥27 ዘዳ14፥29፤ ኢዮ31፥16፡17፡21፤ መዝ146፥9፤ ኢሳ1፥17፡23፤ማቴ25፥36፤ሮሜ12፥2፤ ያዕ4፥4፤2ጴጥ1፥4፤2፥20
2፥1 ቀ፦9፤ ዘሌ19፥15፤ዘዳ1፥17፤ምሳ24፥23፤ሐሥ7፥2፤ 10፥34፤1ቆሮ2፥8
2፥4 ዮሐ7፥24
2፥5 ኢዮ34፥19፤ ማቴ25፥34፤ሉቃ12፥21፤1ቆሮ1፥26-28፤ያዕ1፥12፡16፡19፤ ራእ2፥9

መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም
ድኾች አልመረጠምን? 6እናንተ ግን ድኾ
ችን አዋረዳችሁ፤ እናንተን የሚያስጨንቋችሁ
ሀብታሞች አይደሉምን? ወደ ፍርድ ቤት
የሚጐትቷችሁስ እነርሱ አይደሉምን? 7በእ
ናንተ የተጠራውን ክቡር የሆነውን ስም
የሚሳደቡ እነርሱ አይደሉምን?
8በመጽሐፍ፣ “ባልንጀራህን እንደ ራስህ
አድርገህ ውደድ” ተብሎ የተጻፈውን ክቡር
ሕግ ብትፈጽሙ መልካም እያደረጋችሁ
ነው። 9አድልዎ ብታደርጉ ግን ኀጢአት
መሥራታችሁ ነው፤ በሕግም ፊት እንደ
ሕግ ተላላፊዎች ትቈጠራላችሁ፤ 10ምክንያ
ቱም ሕግን ሁሉ የሚፈጽም ነገር ግን በአ
ንዱ የሚሰናከል ቢኖር፣ ሁሉን እንደ ተላ
ለፈ ይቈጠራል። 11“አታመንዝር” ያለ እርሱ
ራሱ “አትግደልም” ብሎአልና። ባታመነ
ዝር፣ ነገር ግን ብትገድል፣ ሕግ ተላላፊ
ሆነሃል።
12ስትናገሩም ሆነ ስታደርጉ ነጻነት በሚ
ሰጠው ሕግ እንደሚፈረድባቸው ሰዎች
ሁኑ፤ 13ምክንያቱም ምሕረት ያላደረገ ሁሉ
ያለ ምሕረት ይፈረድበታል፤ ምሕረት በፍ
ርድ ላይ ያይላል።

## እምነትና ሥራ

14ወንድሞቼ ሆይ፤ አንድ ሰው እምነት
አለኝ ቢል ሥራ ግን ባይኖረው ምን ይጠቅ
መዋል? እንዲህ ያለው እምነት ሊያድነው
ይችላልን? 15አንድ ወንድም ወይም አንዲት
እኅት የሚለብሱት ልብስም ሆነ የሚመገቡት
ምግብ አጥተው፣ 16ከእናንተ መካከል አንዱ፣
“በሰላም ሂዱ፤ አይብረዳችሁ፤ ጥገቡ” ቢላ
ቸው፣ ለሰውነታቸው ግን የሚያስፈልጋቸውን
ባይሰጣቸው፣ ምን ይጠቅማቸዋል? 17እንዲሁ
ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው።
18ነገር ግን አንድ ሰው “አንተ እምነት
አለህ፤ እኔ ሥራ አለኝ” ይላል። እምነትህን
ከሥራ ለይተህ አሳየኝ፤ እኔም እምነቴን
በሥራዬ አሳይሃለሁ። 19አንድ እግዚአብሔር
እንዳለ ታምናለህ፤ መልካም ነው፤ አጋንን
ትም ይህንኑ ያምናሉ፤ በፍርሀትም ይንቀጠ
ቀጣሉ።
20አንተ ከንቱ ሰው! እምነት ያለ ሥራ
ዋጋ የሌለው[ሀ] መሆኑን ለማወቅ ማስረጃ ትፈ
ልጋለህን? 21አባታችን አብርሃም ልጁን
ይስሐቅን በመሠዊያው ላይ ባቀረበ ጊዜ
በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? 22በዚህም እም
ነት ከሥራው ጋር አብሮ ይሠራ እንደነ
በር ታያለህ፤ እምነትም በሥራ ፍጹም ሆነ።
23“አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም
ሆኖ ተቈጠረለት” የሚለው የመጽሐፍ ቃል

2፥6 ሐሥ8፥3፤
16፥19፤1ቆሮ11፥22
2፥8 ዘሌ19፥18፤
ማቴ5፥43
2፥9 ቀኊ1፤ዘዳ1፥17
2፥10 ማቴ5፥19፤
ገላ3፥10፤5፥3፤ያዕ3፥2
2፥11 ዘፀ20፥13፡
14፤ዘዳ5፥17፡18
2፥12 ማቴ16፥27፤
ያዕ1፥25
2፥13 ማቴ5፥7፤
9፥13፤12፥7፤18፥32-35፤
ሉቃ6፥37
2፥14 ማቴ7፥26፤
ያዕ1፥22-25
2፥15 ማቴ25፥35፡36
2፥16 ሉቃ3፥11፤
1ዮሐ3፥17፡18
2፥17 ቀኊ20፡26፤
ገላ5፥6
2፥18 ማቴ7፥16፡17፤
ሮሜ3፥28፤ዕብ11፤
ያዕ3፥13
2፥19 ዘዳ6፥4፤
ማቴ8፥29፤ማር12፥29፤
ሉቃ4፥34፤1ቆሮ8፥4-6
2፥20 ቀኊ17፡26
2፥21 ዘፍ22፥9፡12
2፥22 ዕብ11፥17፤
1ተሰ1፥3
2፥23 ዘፍ15፥6፤
2ዜና20፥7፤
ኢሳ4፥8፤ሮሜ4፥3
2፥25 ዕብ11፥31
2፥26 ቀኊ17፡20
3፥1 ማቴ7፥1፤
ሮሜ2፥21፤ኤፌ4፥11
3፥2 1ነገ8፥46፤
መዝ39፥1፤ምሳ10፥19፤
ማቴ12፥37፤
ሮሜ3፥9-20
ያዕ1፥26፤2፥10፤
1ጴጥ3፥10፤1ዮሐ1፥8
3፥3 መዝ32፥9
3፥5 መዝ12፥3፡4፤
73፥8፡9
3፥6 ምሳ16፥27፤
ማቴ5፥22፤
15፥11፡18፡ 19
3፥8 መዝ140፥3፤
ሮሜ3፥13
3፥9 ዘፍ1፥26፡27፤
1ቆሮ11፥7
3፥12 ማቴ7፥16

ተፈጸመ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተባለ።
24እንግዲህ በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ
እንዲጸድቅ ታያላችሁ።
25እንዲሁም ጋለሞታዪቱ ረዓብ መልእክ
ተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻ
ቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? 26ከመን
ፈስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ ከሥራም
የተለየ እምነት የሞተ ነው።

## አንደበትን መግታት

3 ወንድሞቼ ሆይ፤ ከእናንተ ብዙዎች
አስተማሪዎች አይሁኑ፤ ምክንያቱም
እኛ አስተማሪዎች የሆንን የባሰ ፍርድ
እንደምንቀበል ታውቃላችሁ። 2ሁላችንም
በብዙ ነገር እንሰናከላለን፤ በንግግሩ የማ
ይሰናከል ማንም ሰው ቢኖር እርሱ ሰውነ
ቱን ሁሉ መቈጣጠር የሚችል ፍጹም ሰው
ነው።
3ፈረሶች እንዲታዘዙልን ልጓም በአፋ
ቸው ውስጥ ስናስገባ፣ መላ ሰውነታቸውን
መምራት እንችላለን። 4ወይም መርከቦችን
ተመልከቱ፤ ምንም እንኳ እጅግ ትልቅና
በኀይለኛ ነፋስ የሚነዱ ቢሆኑም የመርከቡ
ነጂ በትንሽ መሪ ወደሚፈልገው አቅ
ጣጫ ይመራቸዋል። 5እንዲሁም ምላስ ትንሽ
የሰውነት ክፍል ሆና ሳለ በታላላቅ ነገሮች
ትኵራራለች፤ ትልቅ ጫካ በትንሽ እሳት
እንዴት ተቃጥሎ እንደሚጠፋ አስተውሉ፤
6ምላስም እንደ እሳት ናት፤ በሰውነት ክፍ
ሎቻችን መካከል የምትገኝ የክፋት ዓለም
ናት፤ ሰውነትን ሁሉ ታረክሳለች፤ ደግሞም
የፍጥረትን ሩጫ ታቃጥላለች፤ ራሷም
በገሃነም ትቃጠላለች።
7ማናቸውም ዐይነት እንስሳ፣ አዕዋፍ
እንዲሁም በምድር ላይ የሚሳቡና፣ በባሕር
ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ መገራት
ችለዋል፤ በሰውም ተገርተዋል። 8ነገር ግን
ምላስን መግራት የሚችል ማንም ሰው
የለም፤ የሚገድል መርዝ የሞላባትና ዕረፍት
የሌላት ክፉ ነገር ናት።
9በምላሳችን ጌታንና አብን እንባርካለን፤
በእርሷም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትን
ሰዎች እንረግማለን። 10ከአንድ አፍ በረከትና
መርገም ይወጣሉ፤ ወንድሞቼ ሆይ፤ ይህ
ሊሆን አይገባም። 11ከአንድ ምንጭ ጣፋጭ
ውሃና መራራ[ለ] ውሃ ይመነጫልን? 12ወን
ድሞቼ ሆይ፤ በለስ ወይራን ወይንም በለስን
ሊያፈራ ይችላልን? እንዲሁም ከጨው ውሃ
ጣፋጭ ውሃ ሊገኝ አይችልም።

[ሀ]20 አንዳንድ ጥንታዊ ያለሆኑ ቅጆች፣ *ሙት* ይሉታል
[ለ]11 በግሪኩ፣ *ጨው*

## ሁለት ዐይነት ጥበብ

13ከእናንተ መካከል ጥበበኛና አስተዋይ
የሆነ ሰው ማን ነው? ሥራውን ከጥበብ
በሆነ በመልካም አኗኗር ያሳይ። 14ነገር ግን
መራራ ቅንአትና ራስ ወዳድነት በልባችሁ
ቢኖር ከኵራት አይሰማችሁ፤ እውነትንም
አትካዱ። 15እንዲህ ያለችዋ ጥበብ ከላይ
አይደለችም፤ ነገር ግን ከምድር ከሥጋና
ከአጋንንት ናት። 16ቅናትና ራስ ወዳድነት
ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ
ሁሉ ይገኛሉ።
17ከሰማይ የሆነችው ጥበብ ግን በመጀ
መሪያ ንጽሕት ናት፤ በኋላም ሰላም ወዳድ፣
ታጋሽ፣ እሺ ባይ፣ ምሕረትና መልካም ፍሬ
የሞላባት፣ አድልዎና ግብዝነት የሌለባት
ናት። 18የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደ
ርጉ በሰላም ይዘራል።

## ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ

4 በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ
ከየት የመጣ ነው? በውስጣችሁ ከሚ
ዋጉት ምኞታችሁ አይደለምን? 2ትመኛላ
ችሁ፤ ነገር ግን አታገኙም። ትገድላላችሁ፤
በብርቱም ትመኛላችሁ፤ ልታገኙም አትች
ሉም። ትጣላላችሁ፤ ትዋጋላችሁ፤ አትለም
ኑምና ለእናንተ አይሆንም።
3ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳ
ችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት
ትለምናላችሁና።
4አመንዝሮች ሆይ፤ ከዓለም ጋር ወዳጅ
መሆን የእግዚአብሔር ጠላት መሆን እንደ ሆነ
አታውቁምን? ስለዚህ የዓለም ወዳጅ መሆን
የሚፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖ
አል። 5ወይስ በውስጣችን ያሳደረው መን
ፈስ አብዝቶ ይቀናል[ሐ] በማለት መጽሐፍ
የተናገረው በከንቱ ይመስላችኋልን? 6ነገር
ግን ጸጋን አብዝቶ ይሰጠናል፤ መጽሐፍም፣
"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤
ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል"
ያለው ስለዚህ ነው።
7እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤
ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸ
ሻል። 8ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፤ እርሱም ወደ
እናንተ ይቀርባል። እናንተ ኀጢአተኞች እጃ
ችሁን አንጹ፤ እናንተ በሁለት ሐሳብ የምት
ዋልሉ ልባችሁን አጥሩ። 9ተጨነቁ፤ እዘኑ፤
አልቅሱም። ሳቃችሁ ወደ ኀዘን፣ ደስታችሁም
ወደ ትካዜ ይለወጥ። 10በጌታ ፊት ራሳችሁን
አዋርዱ፣ እርሱም ከፍ ከፍ ያደርጋችኋል።
11ወንድሞች ሆይ፤ እርስ በርሳችሁ አትወነ
ጃጀሉ፤ ወንድሙን የሚወነጅልና በወንድ
ሙም ላይ የሚፈርድ በሕግ ላይ ክፉ ይና
ገራል፤ በሕግም ላይ ይፈርዳል። በሕግ ላይ
ብትፈርድ ፈራጅ እንጂ ሕግን አድራጊ
አይደለህም። 12ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ
አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ሊያድንና ሊያ
ጠፋ የሚችል ነው፤ ነገር ግን በባልንጀራህ
ላይ የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?

## ስለ ነገ መመካት

13እናንተ "ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህች
ወይም ወደዚያች ከተማ እንሄዳለን፤ በእር
ሷም አንድ ዓመት እንቈያለን፤ እንነግዳ
ለን፤ እናተርፋለንም" የምትሉ እንግዲህ ስሙ።
14ነገ የሚሆነውን እንኳ አታውቁም። ሕይወ
ታችሁ ምንድን ናት? ለጥቂት ጊዜ ታይቶ
ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ። 15ይል
ቁንም፣ "የጌታ ፈቃድ ቢሆን እንኖራለን፤
ይህን ወይም ያንን እናደርጋለን" ማለት ይገ
ባችኋል። 16አሁን ግን በትዕቢታችሁ ትመ
ካላችሁ፤ እንዲህ ያለው ትምክህት ሁሉ ክፉ
ነው። 17እንግዲህ መልካም የሆነውን ነገር
ማድረግ እንዳለበት እያወቀ የማያደርግ ሰው
ኀጢአት ያደርጋል።

## ለጨካኝ ሀብታሞች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

5 እንግዲህ እናንተ ሀብታሞች ስሙ፤
ስለሚደርስባችሁ መከራ አልቅሱ፤ ዋይ
ዋይም በሉ። 2ሀብታችሁ ሸግቶአል፤ ልብሳ
ችሁንም ብል በልቶታል። 3ወርቃችሁና
ብራችሁ ዝጎአል፤ ዝገቱም በእናንተ ላይ
ይመሰክራል፤ ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበ
ላዋል፤ ለመጨረሻው ዘመን ሀብትን አከማ
ችታችኋል። 4ልብ በሉ፤ እርሻችሁን ሲያ
ጭዱ ለዋሉ ሠራተኞች ያልከፈላችሁት ደመ
ወዝ በእናንተ ላይ ይጮኻል፤ የአጫጆቹም
ጩኸት ሁሉን ቻይ ወደ ሆነው ጌታ ጆሮ
ደርሶአል። 5በምድርም ላይ በምቾትና በመቀ
ማጠል ኖራችኋል፤ ለዕርድ[መ] ቀን ልባችሁን
አወፍራችኋል። 6እናንተን ያልተቃወሙትን
ንጹሐን ሰዎች ኰንናችኋል፤ ገድላችኋልም።

## በመከራ ውስጥ መታገሥ

7እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ጌታ እስከሚመጣ
ድረስ ታገሡ። ገበሬ መሬቱ መልካምን ፍሬ
እስከሚሰጥ ድረስ እንዴት እንደሚታገሥ፣
የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እንዴት
እንደሚጠባበቅ አስተውሉ። 8እናንተም እን
ዲሁ ታገሡ፤ ልባችሁንም አጽኑ፤ ምክንያ
ቱም የጌታ መምጫ ተቃርቦአል። 9ወንድሞች

3፥13 ያዕ2፥18፤ 1ጴጥ2፥12
3፥14 ቀኍ16፤ 2ቆሮ12፥20፤ያዕ5፥19
3፥15 ቀኍ17፤ 1ጢሞ4፥1፤ያዕ1፥17
3፥16 ቀኍ14፤ ሳ5፥20፡21
3፥17 ሉቃ6፥36፤ ሮሜ2፥9፤1ቆሮ2፥6፤ ዕብ12፥11፤ያዕ1፥17
3፥18 ምሳ11፥18፤ ኢሳ32፥17፤ ሆሴ10፥12፤ ማቴ5፥9፤ሮሜ14፥19፤ ፊል1፥11
4፥1 ሮሜ7፥23፤ ቲቶ3፥9
4፥2 ማቴ5፥21፡22፤ ያዕ5፥6፤1ዮሐ3፥15
4፥3 መዝ18፥41፤ 66፥18፤ማቴ7፥7፤ 1ዮሐ3፥22፤5፥14
4፥4 ኢሳ54፥5፤ ኤር3፥20፤ሆሴ2፥2-5፤ 3፥1፤9፥1፤ዮሐ15፥19 ሮሜ8፥7፤ያዕ1፥27፤ 1ዮሐ2፥15
4፥5 1ቆሮ6፥19
4፥6 ምሳ3፥34፤ ማቴ23፥12
4፥7 ኤፌ4፥27፤ 6፥11፤1ጴጥ5፥6-9
4፥8 መዝ24፥4፤ 73፥28፤119፥113፤ ኢሳ1፥16፤ ኤር4፥14፤ዘካ1፥3፤ ሚል3፥7ዕብ7፥19፤ ያዕ1፥8
4፥9 ሉቃ6፥25
4፥10 ቀኍ6፤ ኢዮ5፥11፤1ጴጥ5፥6
4፥11 ማቴ7፥1፤ ሮሜ1፥30፤ 2ቆሮ12፥20፤ያዕ1፥22፤ 2፥8፤1ጴጥ2፥1
4፥12 ኢሳ33፥22፤ ማቴ7፥1፤10፥28፤ ያዕ5፥9
4፥13 ምሳ27፥1፤ ሉቃ12፥18-20፤ያዕ5፥1
4፥14 ኢዮ7፥7፤ መዝ39፥5፤102፥3፤ 144፥4፤ኢሳ2፥22
4፥15 ሐሥ18፥21 ዮሐ9፥41
4፥16 1ቆሮ5፥6
4፥17 ሉቃ12፥47፤ ሕዝ30፥2፤ሉቃ6፥24፤ 1ጢሞ6፥9፤ ያዕ2፥2-6፤4፥13
5፥1 ኢሳ13፥6፤
5፥2 ኢዩ13፥28፤ መዝ39፥11፤ኢሳ50፥9፤ ማቴ6፥19፡20
5፥3 ቀኍ7፡8
5፥4 ዘሌ19፥13፤ ዳ24፥15፤ኤር22፥13፤ ሚል3፥5፤ሮሜ9፥29
5፥5 ኤር12፥3፤ 25፥34፤ሕዝ16፥49፤ አሞ6፥1፤ሉቃ16፥19
5፥6 ዕብ10፥38፤ ያዕ4፥2 5፥7 ዘዳ11፥14፤ ኤር5፥24፤ ኢል2፥23፤ 1ቆሮ1፥7፤ገላ6፥9 5፥8 1ቆሮ1፥7፤ ሮሜ13፥11
5፥9 መዝ94፥2፤ማቴ24፥33፤1ቆሮ4፥5፤ ያዕ4፥11፡12፤1ጴጥ4፥5

[ሐ]5 *ወይም፣ እግዚአብሔር በውስጣችን እንዲኖር ስላደረገው መንፈስ በቅናት ይመኛል፤ ወይም በውስጣችን እንዲኖረው ያደረገው መንፈስ በቅናት ይመኛል ማለት ነው።*

ሆይ፤ እርስ በርሳችሁ አታጕረምርሙ፤ ያለ
ዚያ ይፈረድባችኋል፤ እነሆ ፈራጁ በበር ላይ
ቆሞአል።
10ወንድሞች ሆይ፤ በጌታ ስም የተናገ
ሩትን ነቢያት የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ
አድርጋችሁ ተመልከቱ። 11በትዕግሥት የጸኑ
ትን የተባረኩ አድርገን እንደምንቈጥር ታው
ቃላችሁ፤ ኢዮብ እንዴት ታግሦ እንደ ጸና
ሰምታችኋል፤ ጌታም በመጨረሻ ያደረገለ
ትን አይታችኋል። ጌታ እጅግ ርኅሩኅና
መሓሪ ነው።
12ከሁሉም በላይ ወንድሞቼ ሆይ፤ በሰማይ
ወይም በምድር ወይም በማናቸውም ነገር
ቢሆን አትማሉ፤ "አዎ" ቢሆን አዎ ይሁን፤
"አይደለም" ቢሆን አይደለም ይሁን፤ ያለ
ዚያ ይፈረድባችኋል።

### ከእምነት የሆነ ጸሎት

13ከእናንተ መካከል በመከራ ውስጥ ያለ
አለ? እርሱ ይጸልይ፤ የተደሰተ አለ? የምስ
ጋና መዝሙር ይዘምር። 14ከእናንተ መካከል
የታመመ ሰው አለ? የቤተ ክርስቲያን ሽማ
ግሌዎችን ይጥራ፤ እነርሱም በጌታ ስም
ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። 15በእምነት
የቀረበ ጸሎት የታመመውን ሰው ይፈው
ሰዋል፤ ጌታም ያስነሣዋል፤ ኀጢአትም ሠርቶ
ከሆነ፣ ይቅር ይባላል። 16ስለዚህ ኀጢአታ
ችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወ
ሱም ዘንድ አንዱ ለሌላው ይጸልይ። የጻ
ድቅ ሰው ጸሎት ኀይል አለው፤ ታላቅ
ነገርም ያደርጋል።
17ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ፤ ዝናብ
እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፤ በምድርም ላይ
ሦስት ዓመት ተኩል ዝናብ አልዘነበም።
18እንደ ገናም ጸለየ፤ ዝናብም ከሰማይ
ዘነበ፤ ምድርም ፍሬዋን ሰጠች።
19ወንድሞቼ ሆይ፤ ከእናንተ አንዱ ከእ
ውነት ቢስትና ሌላው ቢመልሰው፣ 20ይህን
አስተውሉ፤ ኀጢአተኛን ከተሳሳተበት መን
ገድ የሚመልስ ሰው ነፍሱን ከሞት ያድ
ነዋል፤ ብዙ ኀጢአትንም ይሸፍናል።

5፥10 ማቴ5፥12
5፥11 ዘፀ34፥6፤ ዘኍ14፥18፤ ኢዩ1፥21፡ 22፤2፥10፤42፥10፡ 12-17፤ መዝ103፥8፤ ማቴ5፥10፤ ዕብ10፥36
5፥12 ማቴ5፥34-37
5፥13 መዝ50፥15፤ ቈላ3፥16
5፥14 መዝ23፥5፤ ኢሳ1፥6፤ማር6፥13፤ 16፥18፤ሉቃ10፥34፤ ሐሥ11፥30
5፥15 ያዕ1፥6
5፥16 ማቴ3፥6፤ 7፥7፤ዮሐ9፥31፤ ሐሥ19፥18፤ዕብ12፥13፤ 1ጴጥ2፥24
5፥17 1ነገ17፥1፤ ሉቃ4፥25፤ሐሥ14፥15
5፥18 ነገ18፥41-45
5፥19 ማቴ18፥15፤ ያዕ3፥14
5፥20 ሮሜ11፥14፤ 1ጴጥ4፥8

መ5 ወይም *ለድግስ*